የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ/2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የተመደበለትን በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የጽ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ/የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ጽ/ቤቱ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በጽ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የጽ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት

- የሂሣብ ማመዛዘኛ ሪፖርት
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት

የጽ/ቤቱን የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀትና በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪ እና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደርን አዋጅ ደንብና መመሪያ የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**ገቢ፤**

1. ጽ/ቤቱ በበጀት ዓመቱ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የተሰበሰበው ገቢ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ መሠረት ብር 16,987,269.03 ሲሆን በሂሳብ ሪፖርት ብር 16,983,219.92 ተመዝግቦ በመገኘቱ ብር 4,049.11 ሪፖርት ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

**የተሰብሳቢ ሂሳብ፤**

2. በሂሳብ መደብ 4203 ለሰራተኞች ከተሰጠው ቅድሚያ ክፍያ ከ3 ዓመት በላይ ብር 30,770.07 ሳይወራረድ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከላይ ከተገለጹት በስተቀር በእኛ አስተያየት የመ/ቤቱ የሂሣብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

**ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤**

3. **የቅ/ጽ/ቤቱ የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ኦዲት ሲደረግ፤**
   - 20 ጎማዎች፤ በጣም ብዙ ጋዜጣዎች፤ በጣም ብዙ ኮምፒተሮች፤ ተሽከርካሪ ወንበሮች፤ 1 የውሃ ማጣሪያ፤ 4 የመኪና ልብስ፤ 7 ላፕቶፕ ኮምፒተሮች፤ 4 የተሰፉ ሙሉ ልብስ (ኮትና ሱሪ)፤ 14 የኮምቲውር ቀለም፤ 2 የመሬት ማፅጃ፤ 6 የመኪና ባትሪዎች ፤16 ጠረጴዛዎች፤ 7 ፕሪንተር ፤4 የመኪና ኦዲቱ እንስኪጠናቀቅ ድረስ ያልተወገዱ መሆኑ ታውቋል፡፡

- ጽ/ቤቱ ለተሽከርካሪዎች የሚሞላውን ነዳጅ ለመቆጣጠር የሚጠቀምበት ቅጽ ያዘጋጀ ቢሆንም እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር መጠን ጋር እየተገናዘበ ምዝገባ የማይከናወንና ለሚመለከተው አካል ተገቢው ሪፖርት በየወሩ የማይቀርብ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከሠላምታ ጋር

------------------------

አንድነት ብዙሰው

የኦዲት ሥራ አስኪያጅ

ቀን ፡ ________________